# አርሊንግተን ውስጥ የሚገኙ የCOVID-19 ህክምና (የቫይረስ/አንቲጅን) እና የሰውነት መከላከያ ምርመራ ቦታዎች

ሁለት አይነት የCOVID-19 ምርመራዎች ማለትም—የዲያግኖስቲክና የሰውነት መከላከያ አሉ፡፡ **የዲያግኖስቲክ ምርመራ** የአፍንጫ ወይም የጉሮሮ ፈሳሽ በመውሰድ በአሁኑ ወቅት ኢንፌክሽን ያለብዎ ስለመሆኑ ያሳያል፡፡ **የሰውነት መከላከያ ምርመራ** የደም ናሙና በመውሰድ ቀደም ሲል በነበረብዎ ኢንፌክሽን ምክንያት የሰውነት መከላከያ አቅም ያሉዎ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሁለት አይነት የዲያግኖስቲክስ ምርመራዎች ማለትም— የቫይረስ PCR እና አንቲጅን—ያሉ ሲሆን ሁለቱም የተለያዩ የቫይረስ መመርመሪያ ዘዴ አላቸው፡፡ **የቫይረስ PCR ምርመራዎች** በከፍተኛ ደረጃ ትክክለኛ ሲሆኑ በላብራቶሪ ይካሄዳሉ (የምርመራ ውጤቶቹ ብዙ ቀናትን ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ **ፖዘቲቭ የአንቲጅን ምርመራ ውጤቶች** በከፍተኛ ደረጃ ትክክለኛ ናቸው፤ **ኔጋቲቭ የአንቲጅን የምርመራ ውጤቶች** በቫይረስ PCR ምርመራ አማካኝነት ማረጋገጥን ሊፈልጉ ይችላሉ፡፡ ፈጣን የአንቲጅን ምርመራዎች ውጤት ለመስጠት 15 ደቂቃዎችን ይወስዳሉ፡፡

ብዙ ኩባንያዎች በቤት ውስጥ ለምርመራ የሚሆን ናሙና ለመሰብሰብ የሚያስችሉዎትን የመመርመሪያ እቃ/ኪት ያቀርባሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ ይህንን ድረ ገጽ ይመልከቱ: https://health.arlingtonva.us/covid-19-coronavirus-updates/covid-19-testing/#athometest።

| የአገልግሎት መስጫ ስምና አድራሻ | ስልክ ቁጥር፣ ድረገጽ፣ የስራ ሰአቶች | የምርመራ አይነት | ብቁነት/መስፈርቶች | አስፈላጊ የምርመራ ቀጠሮ | የሚቀርብ የቋንቋ አስተርጓሚ | የመድን ዋስትና የሌላቸው ታካሚዎች ቅበላ | ወጪ<br>ምርመራ የሚሸፈን መሆንና አለመሆኑን ከኢንሹራንስ ኩባንያዎ ጋር ያረጋግጡ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **AllCare Family Medicine and Urgent Care of Arlington**<br>1515 N. Courthouse Rd.,<br>Suite 140<br>Arlington, VA 22201 | 703-812-8200<br>https://allcarefamilymed.com/arlington-va<br>**ሰኞ-ቅዳሜ**: 8am-8pm<br>**እሁድ:** 9am-5pm | የቫይረስ PCR<br><br>አንቲ ቦዲ | • ደረጃ 1: ከምርመራው በፊት የቨርቹዋል የዶክተር ጉብኝት ያስፈልጋል<br>• ደረጃ 2: በ Alexandria, Tysons Corner, ወይም Lorton AllCare (PCR test) በመኪና እያለፉ (PCR test) ወይም የ Arlington ገጽን (Antibody test) ይጎብኙ | አይደለም፣ ለPCR<br><br>አዎ፣ ለአንቲ ቦዲ | ስፓኒሽ | አዎ | • ተቀባይነት ያገኘ የመድን ዋስትና ወይም የመንግስት መታወቂያ: ነጻ<br>• የመድን ዋስትና ወይም የመንግስት ያልሆነ መታወቂያ ማስረጃ: $125<br>• ተቀባይነት ያላገኘ የመድን ዋስትና: $206 |
| **Arlington Mill Community Center**<br>*(Arlington Free Clinic/Arlington County/Virginia Department of Health)*<br>909 S. Dinwiddie St.<br>Arlington, VA 22204 | 703-912-0118<br>health.arlingtonva.us/covid-19-coronavirus-updates/covid-19-testing<br>**ሰኞ-አርብ**: 12pm-5pm<br>ወር በገባ 2ኛ እና 4ኛ ሰኞ: 12pm-7pm<br>በወሩ 1stኛ ቅዳሜ: 10am-2pm | የቫይረስ PCR | • የምርመራ እድሜ 13+<br>• ምንም የዶክተር ትእዛዝ አያስፈልግም<br>• ዝቅተኛ ገቢ፣ የመድን ዋስትና የሌለው ወይም ዝቅተኛ የመድን ዋስትና ያለው<br>• የ Arlington ነዋሪ | አይደለም<br><br>*በአማራጭነት:* ቀድመው መዝገቡ (እንግሊዘኛ, ስፓኒሽ) | ስፓኒሽ | አዎ | ነጻ<br>*(ይህ ቦታ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው፣ የመድን ዋስትና የሌላቸው እና ዝቅተኛ የመድን ዋሰስትና ላላቸው ነዋሪዎች ምርመራ የሚያቀርብ የአካባቢ የሴፍቲ ኔት ክሊኒክ ነው)* |
| **Capitol Travel Medicine**<br>3800 North Fairfax Dr., Ste. 2<br>Tower Villas<br>Arlington, VA 22203 | 703-351-5100<br>https://capitoltravelmedicine.com<br>**ሰኞ፣ እሮብ፣ አርብ**: 9am-12pm | የቫይረስ PCR<br><br>አንቲጅን<br><br>አንቲ ቦዲ | • ምንም የዶክተር ትእዛዝ አያስፈልግም | አዎ | | አዎ | • PCR: $130<br>• አንቲጅን: $130<br>• አንቲ ቦዲ: $100 |
| **Drive-Through Collection Site**<br>*(Arlington County/Quest)*<br>1429 N. Quincy St.<br>Arlington, VA 22207 | health.arlingtonva.us/covid-19-coronavirus-updates/covid-19-testing<br>**ሰኞ-አርብ**: 9am-4pm | የቫይረስ PCR | • የምርመራ እድሜ 13+<br>• ለምርመራው የዶክተር ማዘዣ ያስፈልጋል<br>• ምልክቶች መታየት አለባቸው | አይደለም | | አይደለም | የምርመራ ክፍያው ለመድን ዋስትና ይሰጣል<br>*(የጤና መድን ዋስትና መቅረብ አለበት)* |
| **INOVA Urgent Care – North Arlington**<br>4600 Lee Hwy.<br>Arlington, VA 22207 | 571-492-3080<br>www.inova.org/locations/inova-urgent-care-north-arlington<br>**ሰኞ-አርብ:** 8am-8pm | የቫይረስ PCR | • ምልክቶች መታየት አለባቸው ወይም<br>• ለቅድመ የቀዶ ህክምና ምርመራ የዶክተር ማዘዣ ያስፈልጋል | አዎ | ስፓኒሽ | አዎ | • ይጎብኙ (አስፈላጊ ከሆነ): $200<br>• PCR: $50 |
| **Preston's Pharmacy**<br>5101 Lee Hwy.<br>Arlington, VA 22207 | 703-522-3412<br>http://prestonspharmacy.com/covid<br>**ሰኞ-አርብ:** 7:30am–5pm<br>**ቅዳሜ:** 8:30am-3:45pm | የቫይረስ PCR<br>አንቲጅን<br>አንቲ ቦዲ | • የምርመራ እድሜ 2+<br>• ምንም የዶክተር ትእዛዝ አያስፈልግም | አዎ | ስፓኒሽ፣ የቬትናም ቋንቋ፣ ቻይኒኛ፣ ራሺያኛ | አዎ (የ2-ቀናት እና የቀጣዩ ቀን ምርመራዎች) | • PCR 3-5 ቀናት: $45 የመመዝገቢያ ክፍያ◊; የምርመራ ክፍያው በመድን ዋስትና ይሸፈናል ወይም፣ መድን ዋስትና ከሌለ በ SSN በነጻ ይሸፈናል<br>• PCR 2-ቀናት: $200◊<br>• PCR ቀጣይ ቀን: $350◊<br>• PCR የዛኑ ቀን: $800◊<br>• አንቲጅን: $199◊ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | • አንቲ ቦዲ: $45 የመመዝገቢያ ክፍያ◊; የምርመራ ክፍያው በመድን ዋስትና ይሸፈናል ወይም፣ መድን ዋስትና ከሌለ በ SSN በነጻ ይሸፈናል |
| **Urgent Care Center of Arlington**<br>2439 N. Harrison St.<br>Arlington, VA 22207 | 571-210-3161<br>www.urgentcarearlingtonva.com<br>**ሰኞ-እርብ**: 10am-6pm<br>**ቅዳሜ/እሁድ፡** 10am-4pm | የቫይረስ PCR<br><br>አንቲጅን | • ምንም የዶክተር ትእዛዝ አያስፈልግም | አዎ | ስፓኒሽ | አዎ | • ይትብኙ (ያስፈልጋል): የጋራ ክፍያ ወይም $150<br>• PCR ወይም አንቲጅን: $50 |
| **Xpress Care**<br>1409 S. Fern St.<br>Arlington, VA 22202 | 703-521-2121<br>https://www.xpresscarenow.com<br>**ሰኞ-እርብ**: 9am-8pm<br>**ቅዳሜ/እሁድ፡** 9am-4pm | የቫይረስ PCR<br><br>አንቲ ቦዲ | • ምንም የዶክተር ትእዛዝ አያስፈልግም | አይደለም | ስፓኒሽ | አዎ | • PCR: $175<br>• አንቲ ቦዲ: $150 |

◊ የመድን ዋስትና ሽፋን የሌለው; በምርመራው ወቅት የሚከፈል

# ልንከተላቸው የሚገቡ የCOVID-19 የምርመራ ደረጃዎች

## 1 ምልክቶቹን ያረጋግጡ

እጅግ የተለመዱት የCOVID-19 ምልክቶች >100.4°F, ትኩሳት፣ ትንፋሽ ማጠር ወይም ለመተንፈስ መቸገር ናቸው

ሌሎች ምልክቶቹ ብርድ ብርድ ማለት፣ በተደጋጋሚ በብርድ መንቀጥቀጥ፣ የጡንቻ ህመም፣ ራስ ምታት፣ የጉሮሮ መከርከር ወይም አዲስ የሚፈጠር የጣዕም ማጣት ወይም ማሽተት አለመቻልን ያጠቃልላሉ።

እንደ ለመተንፈስ መቸገር፣ የደረት ህመም ወይም ግፊት፣ መጫጫን ወይም ለመንቃት አለመቻል፣ ወይም የከንፈር ወይም ፊት መገርጣት የመሳሰሉ የአደጋ ምልክቶች ከታዩብዎ ወደ 911 ይደውሉ።

የትኛውም ያለ አደጋ ምልክቶች ምልክቶቹ የሚታዩበት ሰው በተለይም እድሜው ከ65 አመት በላይ የሆነ ሰው፣ ነፍሰ ጡር ሴት፣ እንደ ስኳር በሽታ ያሉ ከባድ የህክምና ችግሮች ያሉበት ሰው ወይም በከፍተኛ ስጋት ምድብ ውስጥ የሚገኝ ሰው ደረጃ 2ን መቀጠል አለበት።

## 2 ማጣሪያ ያድርጉ

**ዶክተር ካሉዎ**: በአካል ወይም በኦንላይን ማጣሪያ ለማድረግ ቀጠሮ ይያዙ። ሌሎችን ለመከላከል ወደ ዶክተርዎ በቅድሚያ ሳይደውሉ አይሂዱ።

**ዶክተር ወይም የመድን ዋስትና ከሌሉዎ**: በዚህ ሰነድ ላይ ከተዘረዘሩት ክሊኒኮች መካከል ወደ አንዱ ይደውሉ።

በአካል ማጣሪያ ከተደረገልዎ እና ዶክተሩ COVID-19 የለብዎትም ብሎ ከወሰነ ዶክተርዎ የሚሰጥዎትን መመሪያ ይከተሉ።

**ማጣሪያ ካልተደረገልዎ እና ምርመራ የሚያስፈልግዎ ከሆነ** ዶክተሩ ወይም ክሊኒኩ ለእርስዎ የቀጠሮ የጊዜ ሰሌዳ ይይዝልዎታል ወይም ወደ ምርመራ ቦታ ይመራዎታል። አብዛኞቹ የምርመራ ቦታዎች ወደ ምርመራ ቦታዎች የማሽከርከሪያ እና የእግር ጉዞ አማራጮች ያቀርቡልዎታል።

**ምርመራ ማድረግ ያለበት ማን ነው: ከተለመዱት የበሽታው ምልክቶች መካከል የትኛውም ከታዩብዎ ወይም በ COVID-19 ከተያዘ ሰው ጋር ለ15 ደቂቃዎች ያክል ወይም በ6 ጫማ ርቀት ውስጥ ከተገናኙ ምርመራ ያድርጉ።** COVID-19 በመጠነኛ ምልክቶች፣ በከባድ ምሎክቶች ወይም ያለ ምንም ምልክቶች መታየት ሊከሰት ይችላል። የ COVID-19 ምርመራ ማድረግ በታመሙበት ወቅት እራስዎን ለመንከባከብ እና ጓደኞችዎንና የሚወዷቸውን ሰዎች ከህመሙ ለመከላከል የተሻለ ነው። ምርመራ ለማድረግ በጣም ጥሩው ጊዜ ለበሽታው ለመጨረሻ ጊዜ ተጋላጭ ከሆኑበት ቀን በኋላ ከ5 ወይም ከዛ በላይ ቀናት በኋላ ነው።

**አብዛኞቹ የምርመራ ቦታዎች ቅድመ ማጣሪያ ወይም የዶክተር ማዘዣ የሚጠይቁ ሲሆን አብዛኞቹ ደግሞ ቀጠሮ ማስያዝ ይፈልጋሉ።**

## 3 ናሙና ይስጡ

ሁለት አይነት የዲያግኖስቲክስ ምርመራዎች ማለትም—የቫይረስ እና አንቲጅን—ምርመራዎች ያሉ ሲሆን ሁለቱም የተለያዩ የቫይረስ መመርመሪያ መንገዶች አሏቸው። የቫይረስ PCR ምርመራ እጅግ ትክክለኛ ከመሆኑም በተጨማሪ የአፍንጫ ወይም የአፍ ፈሳሽ መውሰድን ይጨምራል።

## 4 ውጤቶቹን ይቀበሉ

ውጤቶቹ ሲደርሱ ይገለጽልዎታል።

ውጤቶቹን በሚጠባበቁበት ወቅት በቤት ውስጥ መቆየትዎና ከሌሎች መራቅዎ እንዲሁም ማህበራዊ ርቀትን መጠበቅ አስቸጋሪ በሚሆንበት ሁኔታ የፊት መሸፈኛዎችን መልበስዎ አስፈላጊ ነው።

በ COVID-19 ከተያዙ እራስዎን እና ሌሎች ሰዎችን ለመጠበቅና የቅርብ ንክኪ/ግንኙነት ያደረጉባቸውን ሰዎች ለመለየት እንዲረዳዎ ተጨማሪ መመሪያ ይሰጥዎታል።

አብዛኞቹ በ**COVID-19** የሚያዙ ሰዎች በራሳቸው በቤት ውስጥ በመቀመጥ ከበሽታው ያገግማሉ።

የ COVID-19 ምርመራ ውጤትዎ ፖዘቲቭ ከሆነ ወይንም ምርመራ ካላደረጉ እና የመተንፈሻ አካል ህመም ምልክቶች የሚሰሙዎ ከሆነ በቤት ውስጥ ይቆዩ እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት አያድርጉ፤ ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚገናኙበት ወቅት የፊት መሸፈኛ ይልበሱ፤ እጆችዎን በተደጋጋሚ ይታጠቡ፤ የነኳቸውን ቦታዎች በቋሚነት ከብክለት ያጽዱ፣ እንዲሁም ከእርስዎ ጋር በቅርበት ለሚገናኙ ሰዎች መታመምዎን ይንገሯቸው።

*ከፌየርፋክስ ካውንቲ የጤና መምሪያ የተወሰደ*

**COVID-19**ን ለተመለከቱ ጥያቄዎች ለCOVID-19 ሆትላይን በሳምንቱ የስራ ቀናት ውስጥ ከ7am-7pm ሰዐት፣ ቅዳሜ ከ9am-5pm ሰዐት በስልክ ቁጥር 703-228-7999 ይደውሉ።

ARLINGTON
VIRGINIA